የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ትብብር - ዴሞክራሲያዊ ምትሕብባር ትግራ

TIGRIAN ALLIANCE FOR NATIONAL DEMOCRACY

( TAND )

# ኢትዮጵያ በፈተና ላይ፥ የመጨረሻው ይሆን!

ሰሞኑን እነ ኣቶ ኣባይ ጸሃየ ያሉበት 12 የህዝባዊ ወያነ ሓርነት ትግራይ (ህወሓት)
የአመራር አባላት (5 ፖሊትቢሮ፥7 ማ\ኮ) ሉኣላዊነትን ለማተግበር በመንቀሳቀሳቸው በ
አቶ መለስ ዜናዊ ቡድን ከማ\ኮ ኣባልነታቸው ያለኣግባብ መወገዳቸውና ይህ ኣምባ
ገነናዊ እርምጃ የድርጅቱ ሕገ ደንብ የጣሰ በመሆኑ ብዙሃኑ ኣባላት በፅናት እንዲ
ታገሉት የሚማጸን ሰፊ መግለጫ ኣውጥተዋል። እነ ኣቶ መለስ በበኩላቸው የኢህኣ
ዴግን ተለጣፊ ድርጅቶችን በማከል፥ ስብሰባ እየረገጡ ኣስቸገሩን ሲል 12ቱን የሚ
ከስ የመልስ ጽሑፍ በትነዋል። 12ቱም በቁም እስር ይገኛሉ ይባላል።

የፖለቲካ፥ የኣይዲዮሎጂ፥ የውጭ እጅና ህገ ደንባዊ ኣስተዳደርን የሚያስሰው የነ
ኣቶ ኣባይ ጽሑፍ ላይ ትኩረት በማድረግ ኣስተያየታችንን እናቀርባለን። ይኸው
መግለጫው እንደሚያትተው በማ\ኮው ውስጥ ለተፈጠረው ችግር መነሻ በሻዕብያው
ወረራና ኣመካከቱ ላይ መሆኑ ያሰምርበታል። ዝርዝር ውስጥ ሲገባም እንደሚቀጥለ
ው ይላል:-

¨ክረምት 1991 ዓ\ም አሜሪካና የአፍሪቃ አንድነት ድርጅት ያዘጋጁት የመፍትሔ
ሰነድ ሉዓላዊነታችንን ፍጹም ስለማያስክብር የኢህአዴግ ሥራ አስፈጻሚ ተወያይቶ
ውድቅ አደረገው። ለህወሓት ማዕከላዊ ኮሚቴ ቀርቦም 17 ለ 13 በሆነ ድምጽ እን
ደገና ውድቅ ሆኖ ነበር። ጦርነቱ ከተገባደደ በኋላ ጥር 1993 ዓ.ም በአመራሩ ውስ
ጥ በተፈጠረው ችግር ላይ ማዕከላዊ ኮሚቴው ውይይት ቀጠለ። ሉዓላዊነታችንን ያ
ስደፈረ ሰነድ እንድንፈርም ሲገፋ የነበረው ወገን (የነአቶ መለስ) ከመድረክ ውጭ
አሉባልታ ወሬ በመንዛት በተለይ የኮራፕሽን (ሙስና) ና የጸረ ዴሞክራሲያዊነት ጉዳይ
በማንሳት ሉዓላዊነት ለማስከበር ጸንቶ በቆመው ወገን (እነ አቶ ዓባይ) ላይ ስም
የማጥፋትና የመነጠል ዘመቻ አካሄደ። ድርጅታችን የሚያምንበት የብዙሃኑ ዴሞክራሲ
ጥሎ ለብርዥዋው ዴሞክራሲ ማጎብደድም ከጽሁፉና ከውይይቱ ተረዳን። በዚህ መን
ፈስ ፋይዳ ያለው ስብሰባ ማካሄድ ስለማይቻል 12 ማዕከላዊ ኮሚቴ አባላት
የፈረሙበት 2 ነጥብ የያዘ ሃሳብ ለማዕከላዊ ኮሚቴ አቀረብን።

1ኛ. ችግሩን ለመፍታት ኣስቸኳይ ጉባኤ እንዲጠራ፥ ዝግጅቱም በጋራ እንዲካሄድ።
2ኛ. ኮራፕሽን፤ ብልሹ ሥነ ምግባርና በሥልጣን መባለግ የሚያጣራ ኮሚቴ
ተቋቁሞ የማዕከላዊ ኮሚቴ ኣባላት ሁሉም በዚህ ማጣሪያ ኣልፈው ውጤቱ ለጉባኤ
ው ቀርቦ ውሳኔ እንዲሰጥበት ነበር።
ያ ወገን (እነ መለስ) የድርጅቱን ህገ ደንብና የምልአተ ጉባኤ አሠራር በመጣስ ከ
ማዕከላዊ ኮሚቴ አባልነታችሁ ታግዳቹሃል ብሉናል። ይህ ለሻዕቢያና ለውጭ ሃይሎች
ተምበርክኮ ሉዓላዊነታችንን የሚንድ ሰነድ ካልፈረምን የሚል ቡድን ህገደምባችንና
ሥነ ሥርዓትን በመጣስ ድርጅቱን ሙሉ በሙሉ ተቆጣጥሮ የህዝቡንና የሃገርን ጥቅ
ም የሚጻረር አቅጣጫ በማስያዝ ጉዳት ሳያደርስ አብረን እንታገለው...¨ እያለ
በስፋት ያትታል።

ኣለፍ ብሎም ይህ ያልተጠበቀ ሁኔታ በማእከላዊ ኮሚቴ ውስጥ በመከሰቱ
ለድርጅቱ አባላት በሙሉ ይቅርታ ይጠይቃል። ይቅርታ! ይቅርታ የሚለው ቃሉ ራ
ሱ ከነሱ በኩል ለመጀመርያ ጊዜ በመስማታችን ገረመን። ጆሮ ያልለመደው ነገር ሲ
ሰማ ክውታ ይፈጥራልና። ይሁንና ይቅርታ የሚያስጠይቅ ብዙ ብዙ ዓበይት ጉዳዮ
ች ስለአሉ ሁሉም ወገን ቢጀምረውና ቢቀጥልበት ለሁላችንም ይበጃል እያልን ወደ
ዋናው ጉዳይ እንመለስ።

እነ አቶ ዓባይ ፀሃየ ባወጡት ጽሑፍ ላይ ሉኣላዊነትን በማንሳቱ በርግጥ ኣርበኛዊ
ቃና ኣለው። ህዝባችንና ሃገራችን በሻዕብያ ቦምቦች ተደብድበዋልና። የኢትዮጵያ ህዝ
ብ የሚጠይቀው የሉኣላዊነት ጥያቄ ግን ፍጹም ኣያማላም። መቸ ህዝቡ መብቱ ተ
ከብሮ ተጠየቀና ወሰነ። በተጨማሪ ጽሑፉ የህገ ደምብ መከተልና ይቅርታ የመጠየ
ቅ ኣዝማምያም ኣይተንበታል። የኣሁኑ ውዝግብ ከህዝብ ተደብቆ የመስራቱ ዘይቤኣ
ቸውንም እንዲጋለጥ በር ከፍተዋል። ከአቤቱታቸው ባሻገር ጽሑፉ ብዙ የድርጅቱ
ይሁን የአመራሩ፤ የህዝቡ ይሁን የሃገሪቱ ኣሳዛኝ ሁኔታዎችን እንድንገነዘብ ይረዳናል
። እስከዚህ ድረስ የተጓዙበት ሂደት ውስጥ ሳንገባ ለአሁኑ ኣቀራረባቸው በኣዎንታ
ዊ መልክ ማየቱ ይመረጣል።

ኣቀራረባቸውና እምነታቸው መመርመሩ ለጊዜው ኣቆይተን፥ በዋናነት ሃገራችን አደገ
ኛ ሁኔታ ጫፍ ላይ እንዳለችና ህዝባችን ህገ ደምብ በማይገዛውና ሥነ ምግባር በ
ጎደለው አስተዳደር ሥር ወድቆ በስቃይና በጭቆና ላይ እንዳለ ቁልጭ አድርጎ ስለ
ሚያሳየን ለዚሁ ከባድ ጉዳይ ትኩረት እንሰጣለን። በጓዶቻቸው\በግማሽ አካላቸው
ላይ ህገ ስርኣት ኣልባ እርምጃ የሚወስዱ አምባገነኖች በህዝቡና በተቃዋሚው ላይ
ምንኛ እንደሚጨክኑ ለመገንዘብ አዳጋች አይሆንም። ለዓመታት ስንልው የነበረው ሃ
ቅም ይኸው ነው። አምባገነኖች ስንል ስድብ ሲመስላችው የነበሩት ሁሉ ለመሳደብሳ
ይሆን ፖለቲካዊ ይዘታቸውና የአስተዳደር ዘይቤኣቸው ለመግለጽ የምንጠቀምበት
ፖለቲካዊ አምር (ሃሳብ) መሆኑ እንዲገነዘቡልን እግረ መንገዳችንን እንጠቁማለን።

¨ብርሌ ከነቃ አይሆንም ዕቃ¨ነውና በዴሞክራሲያዊ ተሳትፎ ሳይሆን በአምባገነናዊ
ተዋረድ፥በግልጽ ውይይት ሳይሆን በተድበሰበሰ ብልጣብልጥነት፥ በህግ የበላይነት
ሳይሆን ራስን ከህግ በላይ በማስቅመጥ፥ በህገ መንግሥት ሳይሆን በህገ ቡድን፥
ሲሰራ የነበረው የህወሓት\ማሌሊት አመራር ላያንሰራራ ተበጣጥሰዋል። ወደ ነበረበት
ተመልሶ መምጣትም አይችልም። መመለሻው የግልጽና የዴሞክራሲያዊ ውይይት
መንገድ አላበጀማ ! ህግን፥ ዴሞክራሲን፥ መልካም ስነ ምግባርን፥ ወዘተ
የሚያጠናክሩ ህብረተሰባዊ ተቃማት እንዳይኖሩ ኣንቀው ይዘው ኑረዋላ።

በአሁኑ ሰዓት ኩፉኛ በሁለት የተሰነጠቀውን አመራር ለማስታረቅ ሽማግሌዎች ሽርጉ
ድ እያሉ መሆናቸው እንሰማለን። ሽምጋዮቹ ያልገባቸው ነገር ያለ ይመስለናል።
የገባቸው ከሆነም በግብረኣበርነት የሚያስጠይቅ ይሆናል። ይኸውም የጥሉ ሥረ
መሠረት ምንነት ነው። በቅድሚያ አመራሩና ዴሞክራሲያዊ አሠራር፥አመራሩና የሕግ
የበላይነት፥አመራሩና ሰብአዊ መብት ማክበር፥......የተጣሉ ስለሆኑ ማስታረቁ በዚህ
መጀመር ነበረባቸው። ይህ ከሆነ በኋላ የፈለገው የልዩነት ነጥብ ቢነሳ በውይይት
ሥነ ሥርዓትና በአሠራር ደንብ እየተፈታ መዝለቅ ይቻል ነበር። ይህ ባለመሆኑ የ
ፈለገው ያህል ሽማግሌ ቢሰበሰብ የነቃውን ብርሌም ቢጠግን እላይ ከተጠቀሰው ከ
ዴሞክራሲያዊ አሠራር፥ የሕግ የበላይነትና የሰብአዊ መብት መከበር ጋር ዕርቅስላል
ተደረገ ጥገናው ሊጸና ፍጹም አይችልም። ለጊዜው የተጠገነ ቢመስል እንኳ ባገረሽበ
ታና እፍ ባሉ ቁጥር ኣንድ ባንድ ይረግፋል። ጋሪውን ያስቀደሙት
ሽምጋዮች ፈረሱ ነው የሚቀድመው እንላቸዋለን።

ተጨማሪ ጣጣም አለ። አመራሩን ከሁለት የሰነጠቀ ናዳ አይዲኦሎጂያዊ፥ ፖለቲካዊ፥
ሉዓላዊነታዊ፥ ዴሞክራሲያዊ ሥነ ምግባርና፥ የውጭ እጅ ይዘት ያለው ልዩነት መሆ
ኑ ከጽሁፉ መገንዘብ ይቻላል። እነዚህ በዝርዝር የተገልጹት ልዩነቶች የሁለት የተለ
ያዩ ፓርቲዎች መፈጠርን የሚያንጸባርቁ ወይም የሚጠይቁ መሠረታዊ አቋሞች ናቸ
ው። ሁለት ድርጅት መሆን የግድ ቢልም በትግራይ ውስጥ ከህወሓት\ማሌሊት ው
ጭ የሌላ ድርጅት ህልውና ስለማይፈቀድ አንዱ ሌላውን ካልዋጠ በስተቀር አብረ
ው ሊኖሩ አይችሉም። ስለዚህ እርቀ ሃሳቡ እንደመፍትሔ ሊሰራ አይችልም። ሽማግ
ሌዎቹ ይህንን ችግር ቀደም ብለው ያላሰቡበት አሁንም የማይታያቸው ይመስለናል።

ሌላ መታወስ ያለበት ነገር አለ። ሁለቱ ወገኖች በመለስና ስብሓት አስተባባሪነት
ማሌሊት የሚባል ፓርቲ ፈጥረው ማሌሊትን የሚቃወም ብቻ ሳይሆን ጥያቄ እንኳን
ያቀረበ እያሠሩ፥ እያባረሩ፥ እየገደሉ (ተኩሉ ሃዋዝና ሺዎች መሰሎቹን ሳንረሳ)፥
ግፍ በቀላቀለ ሴራ ለዚህ እንደበቁ ኣበጥረው ያውቃሉ። እነዚህ ተቃዋሚን በማጥፋ
ት፥ በማሳደድ፥ በመበተን በተንኮል የተካኑ <ሰዎች> የለመዱትን እኩይ ተግባር ሞ
ያ ብለው እየቀጠሉበት ነው። ኣሁን የመለስ ቡድን እነኣባይን የሚኮረኩመው በተለ
ጣፊዎቹ ድጋፍ መሆኑ ማን ይስተዋል። ግራም ነፈሰ ቀኝ ኣምባገነኖቹ በራሳቸው
እኩይ ተግባር ፖለቲካዊ፥ ህጋዊና፥ ሞራላዊ ብቃታቸው ማሽሽዋል። ስለዚህ ሽምግል
ናው ይህን እውነታ ተቀብሎ ሌላ ኣቅጣጫ መቃኘት ኣለበት እንላለን።

ከዚህም ሌላ አንዳንድ የህዝቡ ሳይሆን የህወሓትᎄማሌሊት ወገኖች ከተለያዩ ምክንያቶ
ች በመነሳት የአመራሩ መከፋፈል በዴሞክራሲያዊ ውይይትና በህገ ደንባቸው መሰረ
ት እንዲፈታ እየጠየቁ ናቸው። የነዚህኞቹ ችግር ደግሞ በሂደት ያልተገነባ ስነ ስር
ኣትና ስነ ምግባር ድንገት ዘንቦ ሊያድናቸው እንደማይችል መገንዘብ አለመቻላቸው
ነው። አመራሩ ዴሞክራሲያዊና ህገ ደምባዊ አሰራር የሚከተል ቢሆን ኖሮማ እዚህ
የመከፋፈል ደረጃም ባልደረሰ ነበር። የትግራይ ህዝብ ተቃዋሚ ድርጅት ይሁን ነጻ
ጋዜጣ ባልተነፈገ ነበር። የኢትዮጵያ ህዝብ ባጠቃላይ የሚተማመንበት ስርኣት መገን
ባት በቻለ ነበር። ኣወቆም ይሁን ሳያውቅ የዚህ ቡድን ኣምባገነናዊ ተፈጥሮ የሚጋ
ርድ ሁሉ ወደ ፍትሃዊ ስርኣት እንዳንሸጋገር የሚያደናቅፍ በህዝቡና በሃገሪቱ ላይ
በደል እየፈጸመ መሆኑ ቢረዳው ደግ ነበር። የፈለገው ምድራዊ ጥገና ቢደረግም፥
ቡድኑ እስካሁን ባሳየው ባህርያትና ኣሁን ባለው ደረጃ ኣመራር ሊሰጥ ኣይችልም።
ኣበቃ።

ይህ ድርጅት 60 ሚሊዮን ኢትዮጵያዊ ሊያስተዳድር ይቅርና የራሱ ድርጅትም በሥነ
ሥርዓትና ራሱ ባወጣው ህገ ደንብ ሊመራ ኣልቻለም። ህዝባዊ አምኔታ የራቀው
ው ቡድን ብጥብጥ ብቻ ነው የሚፈጥረው። በመሆኑም ሃገሪቱ አደገኛ ትንንቅ ው
ስጥ ሳትገባ ብሄራዊ እርቅ ይደረግ ዘንድ ሁሉም ቢወተውቱ የሚበጅ መሆኑ እያሳሰ
ብን ይህ ሳይደረግ ቀርቶ ሃገሪቱ በእርስበርስ ግጭት ብትታመስ ተጠያቂው ለዚሁሰ
በብ የሆነው ቡድን ብቻ ሳይሆን አጃቢውም ጭምር መሆኑ ከወዲሁ እናስገነዝባለን።

<u>የኢትዮጵያ ህዝብ ሆይ!</u>

ለአምባገነኖች ሳትንበረከክ፥ ከከፋፋይ ፖሊሲአቸው ሳይበትንህ፥ በግራም በቀኝም ለ
ሚናፈሰው የጽንፈኞች አስመሳይ ፋከራ ሳትበገር በሰከነ መንፈስ የተጫኑብህን ጭቆ
ናና ሽብር ተቋቁመሃል። ሴራዎችና ትንኮሳዎችን ነቅተህባቸዋል። በአርቆ አሳቢነትህ
በጎረቤቶቻችን (ሱማሌ፥ ሩዋንዳ…) የተፈጠሩትን አውዳሚ ክስተቶች እንዳይጋቡብን
አድርገሃል። በዚህ የትግል ኣቅጣጫ በርትተህ ከገፋህ የመከራህ መጨረሻ ደርሶ
ብሩህ የሰላምና ብልጽግና ወቅት ይጠብቅሃል።

ይሁን እንጂ አሁንም ፈተና ላይ መሆንህን መዘንጋት የለብህም። አምባገነኖቹ ገና
ለህዝባዊ ውሳኔ፥ ለፍትሓዊ ኣስተዳደርና ለስነሥርዓት ተገዥዎች አልሆኑምና ወሳኝ
ትግል ኣሁንም ይጠብቃሃል። ትግልህ በጽንፈኞች እጅ ገብቶና፥ በአምባገኖቹ ላይ
ማትኮሩን ትቶ እርስ በርስህ የምትጋጭበት ሁኔታ ለመፍጠር የማይተኙልህ የውስጥና
የውጭ\የቅርብና የሩቅ ጠላቶች እንዳሉብህ ሳትዘነጋ ህብረትህን አጠናክረህ ወሳኙ
ትግልህን እንድታቀላጥፍ ስንጠይቅ ከጎንህ ቆመን እንደምንታገል እያረጋገጥን ነው።

የኢህአዴግ አመራር ፖለቲካዊ፥ ህጋዊና፥ ሞራላዊ ብቃቱ ስለተሟጠጠ፤ ህዝባዊ
አመኔታ የሌለው መንግሥት ደግሞ በሰላም ሊመራ ስለማይችል፥ ሌላ ኣምባገነን
ሳይተካው፥ የምትቆጣጠረውና የሚያስተማምን የራስህ ሥርዓት ለመፍጠር በህብረት
ተንቀሳቀስ። ያኔ ነው ኣይቀሬው የፈተናህ መጨረሻ! የድል መባቻ !

## የትግራይ ህዝብ ሆይ

ኣንተውኑን ኣፍነው ይዘው በስምህ መላው የኢትዮጵያ ህዝብን ሲበዘብዙና ሲከፋፍሉ የነበሩት ኣምባገነኖች ለራሳቸው እንኳን ባወጡት ህገ ደንብ በስነ ስርኣት መመራት ኣቅታቸው ክፉኛ ተከፋፍለዋል። እነሱ በወፈሩና በከበሩ ኣንተ እንደጠገብክና እንደ ደላህ ኣድርገው በማቅረብ ከተቀረው ኣካልህ የኢትዮጵያ ህዝብ ኣጣልተው፥ ቢሆንላ ቸውም ደም ኣቃብተው ለዘለኣለም ሊገዙህ ብዙ መንገድ ተጉዘዋል። የነሱ ግልባጭ የሆኑት ጽንፈኞች ባንተ ላይ እንዲዘምቱ በዘዴ ኣሰማርተውብሃል።
የሻዕብያ ባንዲራ ኣንግበው ለ8 ኣመታት ያህል ኣብረው እንደረገጡህ ከኛ በላይ ኣንተው ታውቀዋለህ። ስቃይህ እንዳንተው የሚሰማቸው ሃቀኛ ታጋይ ልጆችህ እየከ ፋፈሉ ኣንድ ባንድ በትነዋል፥ ኣስረዋል፥ ገድለዋል። ኣሁንም ይህ ኣራዊታዊ ዘዴ እንደተለመደው እንዲጠቀሙበት በተለይ ስብሓትና መለስ እየወተወቱ ናቸው። እስከ ዚህ ያደረሳቸውን ስልት መጥቀሙን በማመን እርምጃ እንውሰድ ይላሉ። ስልጣናቸ ው እንጂ ሌላው ምናችውም ኣይደለምና ሊቀጥሉበት ይችላሉ።

ባጭሩ ይህ ከፋፋይና ኣጥፊ ኣመራር ፖለቲካዊ፥ ህጋዊና፥ ሞራላዊ ብቃቱ የተሟጠ ጠ፥ ኣጥፍቶ ሊጠፋ ጫፍ ላይ የደረሰ ቡድን መሆኑ ተገንዝበህ ከሃቀኛ ልጆችህ፥ ላንተ ሲል ከሚንከራተተው ሰራዊትህ፥ ትልቁ ኣካልህ ከሆነው ኢትዮጵያዊው ወገንህ በኣንድነትና በእኩልነት ተሳስረህ፤ ለሁላችንን ያቀፈችው ኢትዮጵያ በጠንካራ መሰረት ላይ ለመገንባት ተባብረህ ተነስ። የዘመናት ስቃይህ የሚያከትመው፥ ኣኩሪ ኢትዮጵያ ዊታሪክህ የሚታደሰው፥ በሃገራችን ሰላም የሚወርደው በዚሁ መንገድ ስትታገለው ብ ቻነው።

## ህዝባዊ ወገናዊነት የሚሰማህ ሠራዊት!

ለኢትዮጵያ ሉዓላዊነትና ለህዝቦች መብት መከበር ስትታገል፥ስትሞት፥ስትቆስል፥ስትራ ብ፥ መሪዎችህ ሃብት ሲያግበሰብሱና በስልጣን ሲባልጉ እንደነበር ራሳቸው ተጋልጠ ዋል። የተዋደቅክለት ሉኣላዊነትን እንኳ ማስፈጸምም ተስኖዋቸዋል። አንተን መከታ አርገው ህዝቡን እያስፈራሩ ከህግ በላይ ለመሆን ችለው፥ ኣሳር መከራውን አሳይተ ውታል። ሃቀኛ የህዝቡ ልጆችና የምር ተቃዋሚ ድርጅቶችንም አገር እንዳይገቡ ከል ክለዋል። በዚህ ምክንያት ኣንተ እንጂ እነሱ የማይሞቱበትና የማይቆስሉበት ጦርነት እየቀሰቀሱ መሆናቸውን ኣስተውል።

ባጠቃላይ ኣሁን ስልጣን ላይ የተንጠላጠሉት ኣንተን መከታ አድርገው እንጂ ከህዝ ቡ ጋርማ ተቆራርጠዋል። ኣብቅቶላቸዋል። ይህ ቡድን ፖለቲካዊ፥ ሕጋዊና፥ ሞራላዊ ብቃቱ ተሟጠዋል። ህዝብ ሊያስተዳድርና ሃገር ሊመራ በሁሉም ዘንድ ተቀባይት የለውም። አይችልምም። ሰንብቶ የሚፈጥረው ነገር ካለ አንተ የምትሞትበትና የም ትቆስልበት የርስበርስ ግጭትና ትርምስ መቀስቀስ ብቻ ነው። ስለዚህ አውዳሚ ሁኔታ እንዳይከሰት ከጭቁኑ ህዝብ፥ ከሃገር ወዳድና ዴሞክራሲያዊ ሃይሎች ጎን ተሰ ልፈህ ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መመስረት ትታገል ዘንድ መልእክታችን ይድረስህ። እኛም ከጎንህ ቆመን ለመታገል ዝግጁ ነን።

## ተቃዋሚ ድርጅቶች

የህወሓት_ኢህኣዴግ አምባገነናዊ አመራር ሃገራችን ውስጥ ባሰፈነው ከፋፋይ ስርአት ሃገሪቱን ብቻ ሳይሆን እራሱንም ጭምር እንደከፋፈለ ተመልክተናል። እራሱ በኣንድ ላይ ሊቆም ያልቻለ ቡድን ህዝቡን ሊያስተባብር፥ ሃገርን ወደፊት ሊያራምድና ሊመራ ከቶ አይቻለውም። ዋናው አሳሳቢ ጉዳይም በዚሁ የአመራሩ ትርምስ ሃገራችን አሁን ካልችበት የመከፋፈል ሁኔታ ኣዘቅዝቃ ወርዳ በእርስበርስ ትንንቅ ጭራሹን እንዳትበታትን ነው።

ለቀባሪ ማርዳት ኣይሁንብንና፥ በርግጥ ሃገራችን ከባድ ፈተና ላይ ወድቃለች። ኣደገ ኛ ፈተና! ኣፋጣኝ መልስ የሚጠይቅ ፈተና! በበኩላችን ከህብረት ወደ ውህድት በሚል መልእክት የመፍትሄ ሃሳብ ሰንዝረናል። የበለጠ መፍትሄ ከቀረበም ተቀብለን በጋራ ትግል ለጋራ እድገትና ብልጽግና፥ ለዘላቂ ሰላምና አንድንት እንዲሁም ለዴ ሞክራሲያዊ ስርኣት ግንባታ ቆርጠን ተነስተናል። ስለዚህ በታኝና አውዳሚ ክስትቶ ች **ሳይቀድሙን** መርሆአዊ ስብስብ ፈጥረን ህዝብንና ሃገርን እናድን እንላለን።

የኣምባገነኖቹ ቀብር ተቃርበዋል!

**የኢትዮጵያ ህዝብ ትንሳኤ ደርሰዋል!**

**ት ዴ ት**
14 **መጋቢት** 1993